

ፎቶ - በፀሐይ ንጉሤ

# የኮሮና ቫይረስን ለመከላከል የሚያስችል ፕሮጀክት ይፋ ሆነ

ዘላለም ግዛው

አዲስ አበባ፡- ኮቪድ 19 «የኮሮና ቫይረስን» ለመከላከል በኢትዮጵያና በፊንላንድ መንግሥት ትብብር የሚደገፍ፣ በቀጣይ ስድስት ወራት በአምስት ክልሎች የሚተገበር የመጠጥ ውሃ እና የንጽህና ግንባታ ላይ የሚያተኩር ፕሮጀክት ትናንት ይፋ ሆነ።

የማህበረሰብ መርህ የተፋጠነ የውሃ፣ የንጽህናና የሃይጅን ፕሮጀክት«COWASH» (ኮዋሽ) በፌዴራል ደረጃ ኮዋሽ ቺፍ ቴክኒካል አድቫይዘር ሚስተር አርቶ ስዎሚነን፤ በማህበረሰቡ ውስጥ ኮቪድ 19 «የኮሮና ቫይረስ» ለመከላከል በሚሰራባቸው ወረዳዎች በህብረተሰቡ የዝግጁነት ስራ ትኩረት ተሰጥቶት እንደሚተገበር አብራርተዋል።

ፕሮጀክቱ አማራ፣ ቤኒሻንጉል ጉሙዝ፣ ደቡብ ብሄሮችና ብሄረሰቦች፣ ትግራይ እና ኦሮሚያ ክልሎች ላይ የሚተገበር ሲሆን፤ 600 ሺ ሰዎችን ተጠቃሚ እንደሚያደርግ እና 200 ሚሊዮን ብር እንደሚወጣበት ተጠቁሟል።

ሚስተር አርቶ ዝግጁነት ለመፍጠር በ76 ወረዳዎች 25 ሺ ወጣቶችን አሰልጥኖ እንደሚሰማሩ ጠቁመው፤ እነዚህ ሰልጣኞች 600 ሺ ሰዎችን የተለያዩ ግንዛቤ ፈጠራ ስራ በመስራት የአመለካከት ለውጥ እንዲያመጡ በማድረግ የኮሮና ቫይረስ ወደ ማህበረሰቡ እንዳይገባ የመከላከል ስራ ይሰራል ብለዋል ።

ሚስተር አርቶ ቫይረሱ ቢገባ እንኳን አስፈላጊ የሆኑ የምላሽ ስራዎች እንደሚተገበሩ ጠቁመው፤ አስፈላጊ የአደጋ መከላከያ ቁሳቁሶች በለይቶ ማቆያ እና በማገገሚያ ማእከላት በማቅረብ እገዛ እንደሚደረግ ፤ለማህበረሰቡም አስፈላጊ የአቅርቦትና የምላሽ ስራዎች እንደሚሰሩም ተናግረዋል።

የውሃ ኮሚሽን ኮሚሽነር ዶክተር በሻህ ሞገሴ፤ የነበሩ የእጅ መታጠብና የንጽህና አጠባበቅ ባህል እየቀነሱ መምጣታቸውን ተናግረው፤ ከታችኛው ማህበረሰብ ጋር በቅርበት በመስራት ባለው ልምድ የመከላከያ መንገዶቹ ባግባቡ እንዲተገበሩ በማድረግ ግንዛቤ እንደሚፈጥር ያላቸውን እምነት ገልጸዋል። ውሃ ባግባቡ እንዲያገኙ በማድረግና የተበላሹ ተቋማትን በመጠገንም ንጽህና ባግባቡ እንዲጠበቅ ቅድመ ሁኔታዎችን የማመቻቸት ስራ እንደሚሰራ ተናግረዋል።

በፊንላንድ ኤምባሲ የዋሽ አማካሪ አቶ ገዛኸኝ አለሙ በበኩላቸው፤ በኢትዮጵያና በፊንላንድ መንግስት የጋራ ትብብር የሚተገበር ፕሮጀክት የገጠሩን ማህበረሰብ ያማከለ መሆኑን ገልጸዋል። ሁለተኛውን የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ትግበራን መሰረት በማድረግ መፈጸሙን ጠቁመዋል።

ፕሮጀክቱ ሰኔ ወር ተጠናቅቆ ቀጣዩ ምዕራፍ መቀጠል ይገባው እንደነበር፤ ሆኖም በዓለም አቀፍ ደረጃ በተከሰተው የኮቪድ 19 ምክንያት መራዘሙን ያብራሩት አቶ ገዛኸኝ ፤ ቀጣዩ ምዕራፍ በጥር ወር እንደሚጀምር ተናግረዋል።

ሚስተር አርከ የሦስተኛውን ምዕራፍ የስድስት ወራት ፕሮጀክት ይፋ ሲያደርጉ እንደተናገሩት፤ ባለፉት 25 ዓመታት በተለያዩ ስያሜዎች በፊንላንድ መንግሥት አማካኝነት ሲተገበር መቆየቱን ጠቅሰው፤ ባለፉት ዘጠኝ ዓመታት 17 ሺ አካባቢ የውሃ ተቋማት መገንባታቸውን ተቋማቱ በማህበረሰቡ የሚመራና የሚተዳደር መሆኑን ጠቁመዋል። ትግበራው ማህበረሰቡ የባለቤትነትና የእኔነት ስሜት እንዲያድርበት ማስቻሉን፣ የኢትዮጵያ መንግሥት በገንዘብ አስተዋጽኦ 70 በመቶ ድርሻ ያለው መሆኑንም ነው የጠቆሙት።

50 በመቶ ሴቶች በመሪነት የሚመሩት እና የሚሳተፉበት የሚደረግበት አሰራር መዘርጋቱን፤ በውሃ ተቋማት አስተዳደር ላይ ደግሞ ከ50 እስከ 60 በመቶ በመሪነት እንዲሳተፉ እንደሚሰራ፤ የግል ተቋማትም ዕድል እንደሚሰጣቸው ገልጸው፤ አካል ጉዳተኞችን ያካተተ፣ በሚገነቡ ተቋማት ውስጥ የሃላፊነት ሚና እንዳላቸው እና እነርሱን ያማከለ ግንባታ እንደሚከናወንም አስረድተዋል።

ባለፉት ዘጠኝ ዓመታት ሁለት ነጥብ ሰባት ቢሊየን ብር በሆነ ወጪ አራት ሚሊዮን በላይ የህብረተሰብ ክፍሎችን ተጠቃሚ መሆናቸው ተጠቁሟል።